# ሽምግልናና ይቅርታ ከየት ወዴት?

ደስ የሚል ብሎም የሚያስገርም ጨዋታ እየተከታተልን ነው … የሽምግልናና የይቅርታ ጨዋታ፡፡ ጨዋታው አዲስ ወይም ዘመን አመጣሽ ተቀጥያ ባህል ሳይሆን የጥንት የጥዋት የወላጆቻችን ውርስ የሆነ ወግ ባህላችን ነው፡፡ በመሆኑም ነበር ከግለሰብ አለመግባባት አንስቶ እስከ የየአካባቢ ግጭቶች ሲከሰቱ በአገር ሽማግሌዎች ሽምግልናና በዕርቀሰላም እየዳኙ ቀደምት ወላጆቻችን ግጭቶችን ሲፈቱ ወንድማማችነትንና አንድነትን ሲያዳብሩ የኖሩት፡፡

ይህ አጠቃላይ የሽምግልናና የይቅርታ እውነታ የሕዝባችን ሐቅ ቢሆንም በተለይም ባለፉት መቶ ዓመታት በአራት ኪሎው ቤተመንግሥት ውስጥ የተስተናገዱት መሪዎቻችን ልዩነቶችንና አለመግባባቶችን ለመፍታት የሽምግልናና የይቅርታ አሰራር ሲያልፍ እንኳን አልነካቸውም ነበር ለማለት ያስደፍራል፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹማ ዕርቀሰላም አወረድን ብለው ምለው ከተገዘቱ በኋላ በውስጣቸው ከቋጠሩት ቂም ጋር አድብተው ሁኔታዎችን በመጠበቅ የአመለካከት ተቀናቃኛቸውን አሳደው ሲያጠፉ፣ ወይም ግዞት አስግዘው በስብሶ እንዲሞት ሲያደርጉ፣ ወይም አገር ወገኑን ጥሎ እንዲሰደድ ሲያስገድዱ፤ እኛም ያስተዋልነው ታሪክም የዘገበው የመሪዎቻችን ሐቅ ነው፡፡

ከሰሞኑ የደራውና በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሰፊ መነጋገሪያ ርእስ የሆነው በኢፌዲሪ መንግሥትና በተቃዋሚ ታሳሪ መሪዎች መካከል እየተከወነ ነው የሚባለው የሽምግልናና የይቅርታ ድርድርና ወጣ ገባ ነው፡፡ እንደ አንድ ለአገሩና ለሕዝቡ ቀናዒ የሆነ ዜጋ እኔም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከተቃዋሚ ታሳሪ መሪዎች ጋር የተፈጠረውን የተካረረ ቅራኔ በሽምግልና ሊፈቱ እየተቀራረቡ ነው የሚለውን ዜና ከሰማሁበት ሰዓት ጀምሮ እጅግ አስገርሞኛል፡፡ ግርምቴም ከሁለት አቅጣጫ ነው፡፡

አንድም በውስጥ ችግሮቻችን ላይ በእራሳችን አግባቢዎች ተወያይተንና ተደራድረን ወደ ማግባቢያ ሰነድ በመደረሱ፤ እሰዬው አገራችን በሰላምና በይቅርታ ወደ ጥላቻ ሳይሆን ወደ ሰላማዊ ፖለቲካ፣ ዲሞክራሲና ፍትህ ወደ ሰፈነበት የልማት ጎዳና ታመራለች ከሚል የሕዝቦች ፀሎትና ተስፋ የመነጨ አግርሞት ነው፡፡ እውን በመንግሥትና በታሳሪ ተቃዋሚዎች መካከል የሚስተዋለው የሽምግልና ሂደት ይቅር መባባልን፣ በድያለሁና እክሳለሁን፣ የተንተራሰና ከቂም በቀል የፀዳ ከሆነ!

በመንግሥትና በታሳሪ ተቃዋሚዎች ጎራ የተሰለፋችሁ ሁሉ፤ በሕዝብና በአገር ላይ በፈፀማችሁት አውራ-ዘለል በደልና ግፍ በመፀፀት መሸመጋገላችሁና በሕገ-መንግሥትና በሕግ ተገዝታችሁ ሕዝቡን ለመደበስና ለመካስ መቀራረባችሁ ከሆነ፤ ደግመን ደጋግመን እሰዬው የምንለውና እውነትም ለሚሌኒዬሙ ክብረ በዓላችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቀረበ ስጦታ ሊሰኝ የሚችል ተግባር ይሆናል። ይኸውም እውን የሚሆነው ከስያሜው ከሽምግልናና ከይቅር ስለፈጣሪ ይቅር ስለሕዝብ ይቅር ስለአገር አልፎ በተግባር ሁሉም እራሱን ከሕገመንግሥትና ከሕግ በታች ተገዢ አድርጎ የሕዝቡና የአገሩ ታማኝ አገልጋይ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ይሆናል።

ነገር ግን፤ በሌላ በኩል እጅጉኑ ያሳሰበኝ አግርሞት፤ በሕገመንግሥትና በሕግ ውስጥ ጣልቃ እየገባ የሚታየው የመንግሥት ሽምግልናና ይቅርታ መልክና ቁመና እየለየ ማን ከማን ጋር እያለ ጫን-ያለውን እየመረጠ ነው? ወይንስ መንግሥት እንደ መንግሥት የሚከውነው ማንኛውም ተግባር የሁሉንም ዜጎች ሕገመንግሥታዊ መብት በዕኩልነት በሚያስከብር አፈፃፀም ነው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሻቸው አልታይህ አሉኝ።

በተለይም ሽምግልናና ዕርቅን ይቅር መባባልን በረዥሙ የፖለቲካ ሕይወታቸው ውስጥ ከቶዉኑ ጣልቃ አስገብተውት የማያውቁት፣ ሽምግልናና ይቅርታን የባልና ሚስት ጉዳይ ብቻ መፍቻ አድርገው ገድበው ሲናገሩ የነበሩ መሪ፣ ሽምግልናና ዕርቅ የኢሕአዴግ ባህል አይደለም ሲሉን የነበሩ ... የተከበሩ አቶ መለስ ዜናዊ ... ዘንድሮ ከእነ አቶ ኃይሉ ሻውልና ተከታዮቻቸው ጋር የሽምግልናና የይቅርታ ጉባኤ መቀመጣቸውን ስሰማ፤ አዎ በጣም አስገርሞኛል።

በሚያዝያ ወር 1993 ዓ.ም በአንድ የሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ዣንጥላ ሥር የተሰባሰባችሁ፣ የሕይወት መስዋእትነት ባለቃልኪዳን የትግል ጓዶች፣ እጅግ የመረረና ከልክ ያለፈ የሕይወት ዋጋ የተከፈለበትን ታሪክ በደም የፃፋችሁ መሪዎች፤ አውራ-መንገድ ላይ አመፅ በመቀስቀስ የሕዝብ ደም በማፍሰስ ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት የሓሳብ ልዩነትና መከፋፈል በመከሰቱ ችግራችሁን በሽምግልና እንድትፈቱ የአገር ሽማግሌዎች ቢማፀኗችሁ፤ እጠቅሳለሁ "... ሽምግልና የድርጅታችን ባህል አይደለም ... ጉዳያችን እንደ ባልና ሚስት ጉዳይ በሽምግልና የሚፈታ አይደለም..." በተባለበትና እነዚያን የተከበሩ የትግራይ ሽማግሌዎች ፊት ነስተው እንዳልመለሱ ዛሬ ምን ተፈጠረ? አዲስ የባህርይ ለውጥ? ከዕድሜ ፀጋነት ጋር የመጣ የአስተሳሰብ ብስለት? ወይንስ ለስልጣን ሲባል የደርግ ርዝራዦች ካላችኋቸውና እስከሞት የሚያስቀጣ ክስ ከተጋረጠባቸው ጋር መሞዳሞድ? የትኛውም ሓሳብ አልገባኝም።

ይህንን ያስገረመኝንና ያሳሰበኝን እውነታ እንደመንደርደሪያ በማስቀመጤ አሁን በጀመራችሁት የሽምግልናና የይቅርታ ሂደት ላይ ቅንጣት ታህል ተቃውሞ ወይንም ቅሬታ ኖሮኝ አይደለም። እሰዬው ስለሰላም ስለዲሞክራሲ ስለፍትህና ስለልማት የሚደረግ በጎ ተግባር እስከሆነ ድረስ ብያለሁ።

ነገር ግን ያለፈውስ አለፈ፤ በአሁኗ ሰዓት በኢትዮጵያችን ውስጥ ከፖለቲካ ጋር በተዛመደ ክስ ታስረው የሚገኙትና ችግራቸው በሽምግልናና በይቅርታ መታየት ያለበት እነአቶ ኃይሉ ሻውልና ተከታዮቻቸው ብቻ ናቸውን?

ወይንስ እነዚያ በአንድ ወቅት በአዋሳና በጋምቤላ አካባቢ በተከሰቱ አለመግባባቶችና ግጭቶች ለዓመታት እስራት የተዳረጉት ኢትዮጵያውያን ሽምግልናና ይቅርታ አያስፈልጋቸውም? ወይንስ እነዚያ በተለያየ የኦሮሚያ ፖለቲካ አለመግባባቶች ሳቢያ በየስርቻው በተቋቋሙ የኦሮሚያ ክልል እስር ቤቶች ውስጥ የሚማቅቁት ኢትዮጵያውያን ሽምግልና ይቅርታና ምሕረት አያስፈልጋቸውም? የሜጫና ቱሉማ የኦሮሞ አባቶችስ? እነዚያ በተለያዩ የትግራይ እስር ቤቶች ውስጥ የተለያየ ምክንያት እየተለጠፈባቸው የሕግ ከለላ ተነፍጓቸው በእስራት የሚማቅቁት የትግራይ ተወላጆችስ? ሰሚን ጉድ ያሰኘው የተከበሩ የአቶ ስዬ አብርሃና የቤተሰቦቻቸው ጉዳይስ? በአጠቃላይ እጅግ በርካታ ዜጎች በአመለካከት ልዩነት ብሎም የመናገር የመፃፍ ያመኑበትን የፖለቲካ እምነት በሰላማዊ መንገድ የመግለፅና የማራመድ ... ወዘተ. ሕገመንግሥታዊ መብታቸውን ለመጠቀም በመሞከራቸው ብቻ ለእስራትና ለመጉላላት ብሎም ለስደትና ለእንግልት የተዳረጉት ዜጎች በሽምግልናና በይቅርታ ይሁን ሕገመንግሥቱ ባስቀመጠላቸው መብት ተጠቅመሙ ፍትህ አግኝተው ነፃነታቸውን መጎናፀፍ አይገባቸውምን?

አንዲትና የሁላችንም የዕኩልነትና የአንድነት ቤታችን የሆነችውን እናት አገራችንን የሚያስተዳድር ማንኛውም መንግሥት፤ ዜጎችን በዕኩልነት ሊያየን በሕግ ሊዳኘንና ሊያስተዳድረን፣ ሕገመንግሥታዊ መብታችንን በዕኩልነት አክብሮ ሊያስከብርልን ሲገባ፤ አንዱን ዜጋ ያለኃጢአቱ በሕግ ይዤሃለሁ ብሎ በፈጠራ ክስ ለዓመታት በእስራት ሲያማቅቀውና ቤሰተቦቹም በችግር እንዲበታተኑ ሲያደርግ፤ ሌላውን ደግሞ "... እስከሞት የሚያስቀጣ ወንጀል ብትፈፅምም፣ ፀረ-ሰላም ፀረ-ሕገመንግሥት በአጠቃላይ ፀረ-ሕዝብ ብትሆንም፤ ተሸማግለን ይቅር ብየሃለሁ ..." የሚባልበት ሥርዓት መፍቻ የሌለው እንቆቅልሽ ነው የሆነብኝ።

ምናልባትም መሪዎቻችን ከጊዜያዊ የሥልጣን ጥቅም አኳያ ከውስጥና ከውጭ የተፈጠሩ ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም በሚል ይህንን የቅንጅት ታሳሪ መሪዎች

የሽምግልናና የይቅርታ መንገድ ተከትላችሁ፤ በሌላ በኩል ግን በብዙ መቶዎች የሚቆጠር በየክልሉና በፌዴራል እስር ቤቶች ውስጥ የሚማቅቀውን የፖለቲካ እስረኛ ሽምግልናችሁና የእርቅ አሰራራችሁ የማይመለከተው ከሆነ፤ በሕዝብም በታሪክም ተጠያቂና ተወቃሽ ያደርጋችኋል። ይህም የተዛባ ጎዳና ምናልባት ጊዜያዊ ድል ፈንጠዝያና የፖለቲካ ጥቅምን ሊያስገኝላችሁ ይችል ይሆናል። የዘለቄታው ግን ሰላምን በሕዝብ ተኣማኒነትን አንድነትን የሚያሳጣ ከመሆኑም ባሻገር፤ ኢሕአዴግ እንደ ኢሕአዴግ ጠብቋቸው የተጓዘበትንና የሰፊው ሕዝብ ወገን ነኝ ቆሜለታለሁ የሚላቸውን ድርጅታዊ ባህሪያትን ሳይቀር አሚጦ የሚያጠፋበት ይሆናል እላለሁ።

ታሳሪ የቅንጅት መሪዎች የኢትዮጵያ "የበኩር ልጅ" ሆነው ጫጊና አቤት ባይ ስላላቸው ሽምግልና ይቅርታና ምሕረት እየዘነበላቸው ከተወነጀሉበትና እንደተራራ ገዝፎ ከተነገረለት ጥፋት የሚያጥባቸው ከሆነና፤ በሌላ በኩል ግን ድኃውና የሚጮህለት ሰሚና ነጋሪ የሌለው ብዙሓኑ የኦሮሞ የትግራይ የጋምቤላ የደቡብ ኢትዮጵያ... ወዘተ. የክልሎች ሕዝባችን ግን ሕገመንግስታዊ መብቱን ለመጠቀም ስለሞከረ ብቻ ይቅርታን ተነፍጎ ሕግ ይዳኘዋል በሚል ሽፋን በእስራት የሚማቅቅበት ከሆነ፤ ሕዝቦች ለዘመናት ለመብት ለዕኩልነት የከፈሉትን ዋጋ ከንቱ የሚያስቀር አሳፋሪ ሥርዓት እየተከላችሁ እንደሆነ ከወዲሁ ተገንዘቡት።

ስለዚህ የሽምግልናንና የይቅርታ አሰራርን እንደ አሰራር እውቅና ሰጥታችሁ በሕገመንግሥትና በሕግ ሥርዓት ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ ከፈቀዳችሁ ዘንዳ፤ አፈፃፀሙም ማንኛውንም ዜጋ በዕኩልነት የሚመለከት የሚያሸማግልና ይቅርታን የሚያደርግ መሆን እንዳለበት አስምሩበት እላለሁ። መንግሥትም ሆነ ተቃዋሚዎች፤ ሽምግልናና ይቅርታ ስሕተትና ጥፋትን እየሸፋፈኑ የሙጥኝ ብሎ መንገታገትንና ሕዝብና አገርን ይዞ ከመጥፋት መንገድ የሚመልስ፣ ካለፉት አፀያፊ ድርጊቶች እራስን አስተካክሎ ሕዝብ በሚፈልገውና ሕገመንግሥት በሚፈቅደው ቀና ጎዳና ላይ በመጓዝ ሕዝብን የሚጠቅም ለአገር የሚበጅና ለትውልድ የሚተላለፍ አርአያነት ያለው ፀጋን ማበልፀግ ይመስለኛል።

ሰላምና ፍቅር ለሕዝባችን

**ሰኔ 20/1999**

ካሣ